በረድኤተ መንፈስ ቅዱስ መመራት፦ ጣማፍ ኄራኒ ገና በወጣት ዕድሜዋ ያደረባት የእግዚአብሔር ቅዱሳን፣ የቅብጥ ቤተ ክርስቲያንና የሰማዕታቱ ፍቅር፣ በረኻውያን አባቶች የጻፏቸውን ብዙ መጻሕፍት ለማንበብ ምክንያት ሆኗታል። ለምሳሌ፦ መጽሐፈ ገነት፣ የቅዱስ ዮሐንስ ሳባ፣ የይ ስላቅ ሶርያዊ፣ ቅዱስ ዮሐንስ «St.John Of The ladder»፣ የቅዱስ ያዕቆብ ዘስሩግ ሆሚሊስ መጻሕፍትን መጥቀስ ይቻላል።

ይህን ጥልቅ መሻቷንና የልብ ንጽሕናዋን የሚያውቅ እግዚአብሔር፣ ደብዛው ሊጠፋ የደረሰው የሴቶች ገዳም፣ ዳግም ይነሣ ዘንድ ለማደራጀቱ ሥራ እርሷን መርጦ በአ.ሰ.ሴ.ገ. አስቀመጣት። እርሷም በገዳማዊ ሕይወቷ እጅግ ደስተኛ ነበረች፣ አዘውትራ *«ከምንኩሰና ሕይወት በላይ መልካምና ደስ የሚያሰኝ ነገር የለም። ለኅበውም ሆነ እማት፣ በፍቅርና ራስን በማዋረድ፣ ሕግጋተ እግዚአብሔርንም እየጠበቁና በገዳማዊ ሥርዓት እየተመሩ እንደ መኖር የመሰለና የሚወዳደረው ሕይወት የለም። ገዳማዊ ሕይወት ማለት ገነትን መሬት ላይ እንደ ማየት ነው»* ትል ነበር።

በእርሷ ሕይወት ውስጥ፣ ታላቁ አባት አባ ጳላሞን ለደቀ መዝሙሩ ለአባ ጳኩሚየስ የሰጠውን ትምህርት እናያለን። ይኸውም፦ «እግዚአብሔር ይህንን ገዳም ታላቅና ታዋቂ ታደርገው ዘንድ ሥልጣን እንደ ሰጠህ ተረድቻለሁ። እጅግ ይሰፋል፣ የመነኰሳትና መነኰሳይያት መነኻርያ ይሆናል። ብዙ ነፍሳትም ይድኑበታል። ይህንን ጎላፊነትና አብሮ የሚመጣውንም፣ እስከ የሌለው ፈተና ትቀበለው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው»።

ለጣማፍ ኄራኒም ይህንን ጎላፊነት እግዚአብሔር በጥበቡ ሰጥቷታል። እርሷም ጎላፊነቱን በታላቅ ፍቅር ተቀብላ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሥራዋን ጀመረች። በኣመራር ሥራዋ ሁሉ መደገፊያዋ እምነቷ ብቻ ነበር። ከሕመሟና ከድካሟ በላይ ሆና ራሷን መልካም እርሾ አደረገች። ይህ መልካም እርሾ፣ ለሌሎች ብዙዎች የድኅነት ምክንያት ሆነ። የኣንድነት ኑሮ ወጣኒ ለሆነው ለአባ ጳኩሚየስ ከእግዚአብሔር የተሰጠው ቃል፣ በድጋሚ በጣማፍ ኄራኒ ተፈጸመ። «አትፍራ፣ ብርታት ይኑርህ . . . የእግዚአብሔር እጅ ይመራሃል፣ ለድልም ያበቃሃልና። ወደ አንተ የመጣውን ሁሉ ተቀብለህ ከእግዚአብሔር ጋር ታገናኝ ዘንድ የእርሱ ፈቃድ ነውና»።

ምዕራፍ ሦስት።

«ዳዊትም ልጁን ሰሎሞንን፦ ጠንክር አይዞህ፥ አድርገውም፣ አምላኬ እግዚአብሔር አምላክ ከኣንተ ጋር ነውና አትፍራ፥ አትደንግጥም፣ ለእግዚአብሔርም ቤት አገልግሎት የሚውለውን ሥራ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ እርሱ አይተውህም አይጥልህምም» (፩ኛ ዜና ፳፰፥፳)።

በተቀደሰው መስክ፥ ያለመታከት የተፈጸመ ታላቅ አገልግሎት።

«አቤቱ ሥራችንን ሁሉ ሠርተህልናልና ሰላምን ትሰጠናለህ» (ኢሳ.፳፮፥፲፪)። ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስና፥ ቅዱስ፣ ምስጉን፣ ቡሩክ የሆነ ቸር እግዚአብሔር፣ እናታችን ኄራኒን ከሕክምና ቆይታዋ በኋላ፥ ወደ በኣቷ በሰላም መልሶ አመጣልን። ከዚያ ሁሉ የቀዶ ሕክምና ስቃይ በኋላ፥ በኣዲስ መንፈስና የሥራ ፍላጎት፣ መንፈሳዊውንም፣ የግንባታ ሥራዋንም ለመፈጸም ተዘጋጀች። ከታቀደው ሥራ በተጨማሪ፥ ገዳሙን ለማስፋትና የተግባር ቤቶችን ለማደስ፣ ዕቅድ አወጣች። በተለይ ደግሞ ቊጥራቸው ብዙ የሆኑ ወጣቶች፣ ለኣመክሮ በመምጣታቸው ምክንያት፥ ተጨማሪ በኣቶችን መገንባት በጣም አስፈላጊ ሆነ። ይህ ዐላማ በሰዓቱ ከዓቅም በላይ የሆነ ጥያቄ ቢሆንም፣ እርሷ ግን፥ የገዳሙ ይዞታ የነበረውን መሬት መልሶ መረከብ፥ ልዩ ትኵረት የሰጠችው ጥያቄ ነበር።

የብፁዕ አባታችን ዕረፍት ከሆነበት፣ ከ፲፱፷፬ ዓ.ም. በኋላ፥ የቀጣዩ ፓትርያርክ ምርጫ አል-ቋራህ አል-ሐይካሊያህ (Al-Qur'ah al-Haykaliyyah)[9] ከመኪያሄዱ በፊት፣ ብፁዕ አቡነ እንጦንስ (የኋላው ሊኑዳ ፫ኛ)፥ ከብፁዕ አቡነ ሲኑዳ አል-ሱርያኒ (Al-Suryani) ጋር፣ ወደ አቡ ሰይፊን ገዳም መጥቶ ነበር። እማሆይ ኄራኒ፥ ገዳሙ በጣም ሰፊ መሬት እንደሚያስፈልገው፣ በዚህ አጋጣሚ ነገረቻቸው። አቡነ እንጦንስን ደግሞ፥ ይዛው ወደ ሕንፃው ጣርያ ላይ ወጥታ፣ ቀጣዩ ፓትርያርክ እርስዎ እንደሚሆኑ በሕልሜ አይቻለሁ። አሁንም ወደዚህ ጣርያ ይዤዎ የወጣሁት፣ የቀደመውን ይዞታችንን በደንብ ለማየት ይችሉ ዘንድ ነው። ይህን የምነግርዎም፣ ከኣሁን በኋላ እርስዎ በምርጫው ሥራ ስለሚጠመዱና፥ ሌሎች ብዙ ጎላፊነቶችንም ስለሚረከቡ፣ አግኝቼ ላናግርዎት አልችልምና፣ ከወዲሁ ላሳስብዎ ብዬ ነው። ብፁዕ አባቴ! በቦታ ጥበት ችግር ገጥሞናልና፥ ይህ የመሬት ጉዳይ፣ በእኛ ዘንድ ትልቅ ትኵረት የተሰጠው ጥያቄ ነው አለችው። እርሱም ባነጋገሯ ከሳቀ በኋላ፥ በለሰለሰ አንደበቱ፣ «እንግዲህ አንቺ ስለ እኔ ፕትርክና ተንብየሻል። እኔም ይህንን መሬት ለገዳሙ ለማስመለስ ቃል እገባልሻለሁ» አላት።

ከኣል-አዝሓር ቅ.ጊ.ቤ.ክ. ከመጡት አባቶች አንዱ፥ ስለ አቡነ ሲኑዳ ሹመት

---

[9] እግዚአብሔር ለቤቱ ብቁ የሆነውን ይመርጥ ዘንድ፣ በዕጣ ማውጣት የሚደረግ የፓትርያርክ ምርጫ ሲሆን፥ በኣቃቤ መንበር አማካይነት፥ ለመጨረሻ ምርጫ የቀረበው የሦስቱ ዕጩዎች ሥም በፖስታ ታሽጎ፥ ሣጥን ውስጥ ይደረግና ሣጥኑ ይታሸጋል። በለንበተ ክርስቲያን ከቅዳሴ በፊት ሣጥኑ ተወስዶ መንበረ ፓትርያርኩ ባለበት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንበር ላይ ይቀመጣል። ሥርዓተ ቅዳሴው ከተፈጸመና ቅዱስ ምሥጢር ከተካፈሉ በኋላ፥ ካህኑ ከኣስቀዳሹ ሕዝብ መካከል ሕፃን ልጅ ይመርጣል። የተመረጠው ሕፃን፥ ዐይኑን በመሃረም ይሸፈንና ሣጥኑ ተከፍቶለት ከውስጥ ካሉት ሦስት ፖስታዎች አንዱን እንዲያወጣ ይደረጋል። ያ ያወጣው ፖስታ ላይ ስሙ የተጻፈው አባት ፓትርያርክ ሆኖ ይሾማል። የቀሩት ሁለት ስሞች ይወጡና ለሁሉም በግልጽ እንዲታዩ ይደረጋል። Mounir Choucri, "Paterlarchal Election" The Coptic Encyclopedia, vol.6 ed. Aziz (N.Y: Macmilln Publishing Company, 1991), p.1912።

የነገረችውን ነግሮናል፦ «ቀጣዩ ፓትርያርክ በእናንተ ዘንድ ተወዳጅ የሆነው ብፁዕ አቡነ እንጦንስ ነው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ፥ ከመንበረ ማርቆስ አጠገብ ቆሞ ነበር። ከዚያ ብፁዕ አቡነ እንጦንስ መጥቶ፤ መንበሩ ላይ ተቀመጠ። አቡነ ቄርሎስ ደናም በትረ ሙሴውን ሰጠው። ይህ ሲሆን እመቤታችን አጠገባቸው ነበረች። ከዚያ ርግብ መጥታ፤ በአቡነ ሲኖዳ ራስ ላይ አረፈች» አለችን። ይህንን ሕልም በተደጋጋሚ ማየቷንም ገልጻልናለች። አቡነ ሲኖዳ ለገዳማትና ለምንኩስና ያለውን ጽኑ ፍቅር ስለምታውቅ፤ ሕልሟ እውን ይሆን ዘንድ አጥብቃ ትጸልይ ነበር።

የአንድነት ማኅበሩ አባላት ቊጥራቸው እጅግ እየጨመረ መጣ። የቦታ ችግሩ መፍትሔ እስኪያገኝ ድረስ፤ እማሆይ ኄራኒ ፪ኛና ፫ተኛ ፎቅ ላይ ያሉትን በአቶች እያንዳንዳቸውን ለሁለት ከፈለቻቸው። በዚህ ዘዴም እያንዳንዷ መነኲሲት የራሷ የሆነ ጠባብ በኣት እንዲኖራት ሆነ። አሁንም የወጣንያኑ ቊጥር እየጨመረ በመም ጣቱና በቂ ቦታ ባለመኖሩ፤ በእያንዳንዱ ጠባብ በኣት ውስጥ ቢያንስ ሁለት ሰው መኖር እንዳለበት፤ ለገዳማውያኑ አሳሰበቻቸው። አንዳንዴ አንዱን በኣት ለአራት የሚጋሩበት ጊዜም ነበር። ይህም ሆኖ አንዳንድ ጊዜ፤ ጣማፍ የምድር ቤቱን የእንግዳ ማረፊያ ቤት፤ ለተወሰኑ ወጣንያን በጊዜያዊነት ለመስጠት ትገደድ ነበር። ሌሊት እነርሱ ያድሩበታል። ቀን ደግሞ እንግዳ መቀበያና ማረፊያነቱን ይቀጥላል።

እናት ኄራኒ እስካሁን የተጠቀመችው መፍትሔ አርኪ ባለመሆኑ፤ ሕንፃውን ከባለ ፫ ፎቅነት ወደ ፬ ለማሳደግ ተገደደች። ፬ኛው ፎቅም እንዲሁ በብዙ ትንንሽ በኣቶች ተሸነሸነ። በዚህ ውጤት፥ በነበሩት በኣቶች ላይ፤ ሃያ ተጨማሪ በኣት ማግኘት ተቻለ። ይህ መፍትሔ ከኣጭር ጊዜ መዝለል ባለመቻሉ፤ አሁንም ተመሳሳይ ችግር ከፊቷ ተደቀነ። በዚህ ምክንያት የገዳሙን የቀደመ ይዞታ ለማስመለስ፤ ያልፈነቀሉት ድንጋይ ባይኖርም፤ ብዙ ዕንቅፋቶች ነበሩትና ለጊዜው ሕልሟን እውን ማድረግ ሳትችል ቀረች[10]። ሆኖም በጽኑ እምነቷ፤ በላቀ ምኞቷና በጸሎቷ አጋዥነት፥ ከጊዜያት በኋላ ያቀደችውን ማሳካት ችላለች።

ችግሩ እስኪፈታ ድረስ በነበረው ጊዜ ውስጥ፤ ይመጡ የነበሩትን ወጣንያን ወደ ሌላ ገዳም እንዲሄዱ ትመክራቸው ነበር። አንዳንዶቹን ወደ እመቤታችን፣ ሌሎቹን ደግሞ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ገዳም፤ እንዲሄዱ ትጠቁማቸዋለች። «በእነዚህ ገዳማት ያሉት እመምኔቶች፥ የመንፈስ ልጆቼ ስለሆኑ ሥርዓታችን አንድ ነውና፤ ሥጋት አይግባችሁ» እያለች ብትመክራቸውም፤ አንዳንዶቹ ከኣቡ ሰይፈን ገዳም ሌላ ወደየ

[10] በዘመኑ የቅብጥ መነኲሳይያት ዙሪያ፥ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረበች የደች ባለሙያ፥ «የቦታ ጥበት ችግር፥ በጣ መቱ ወደ ገዳም ሊዝ የሚችሉትን ወጣንያን ቊጥር በእጅጉ ይገድበዋል። ካለች በኋላ፥ እንደ ምሳሌ የጠቀሰችው በአርጌዋ ካይሮ የሚገኘውን የአቡ ሰይፈን የሴቶች ገዳም ነው። ያላቸው የቦታ ገደብ እፍኝ የማይሞሉ ወጣንያንን ብቻ እንዲቀበሉ የሚያስገድድ ቢሆንም፥ እነርሱ ግን በርካታ ቊጥር ያላቸውን ወጣንያን ተቀብለው ያስተናግዳሉ፤ ብላለች። Pietemell Van Doorn, Contemporary Cop-tic Nuns, p.82.

ትም አንሄድም ይሏት ነበር። በዚህ የቦታ ጥበት ምክንያት፤ ወጣንያኑ የሚፈልጉትን ሕይወት ለመወጠን ተቸገሩ። እንዲያውም አንዳንዶቹ እናት ኄራኒ ሆን ብላ፤ ለበብ እየፈለገች ቦታ የለም የምትላቸው ይመስላቸው ነበር።

ከችግሩ አሳሳቢነት የተነሣ፤ ጣማፍ ኄራኒ ከከተማ ወጣ ያለና ጸጥታ የሰፈነበት ሥፍራ ፈልጋ መሬት ለመግዛትና፤ በዚህኛው ገዳም ሥር የሚተዳደርና ሥርዓቱ ሁሉ የዚህኛው ግልባጭ የሆነ፤ ሌላ የአ.ሰ.ሴ.ገ. ለማስገደም ታስብ ጀመር። ስለ ገዳማዊነት ያላት ጽኑ ፍቅርና፤ እንደ ሰደድ እሳት እየተቀጣጠለና እየሰፋ የሚሄደው መንፈሳዊነቷ ወደዚህ አዲስ ዐላማ አመጣት። ከምንም በላይ ጸጥታውና ሰላማዊነቱ ስለሚማርካት፤ በየዓመቱ፥ በረኻውያን ወደሚኖሩበት እየሄደች ትጸልይ ነበር። የበሽታዋ ጽናት፣ የአስተዳደር ጎላፊነትና ለመሬት ጥያቄ የምታደርገው እንቅስቃሴ፤ ይህን በየዓመቱ የምታደርገውን የበረኻ ጉዞ አያስታጉልባትም። መንፈሰ ጠንካራ ለመሆንና ራስን ለመፈተን፤ ያለውን አስተዋጽኦ ስለምታውቅ፤ በረኻ በልቧ ትልቅ ሥፍራ አለው። ከበረኻዎቹ ወደ አንዱ ሄዳ፤ ምንም በማይሰብረው ጸጥታ ውስጥ፥ ሆና ሌሊትና ቀኑን በጸሎት ታሳልፋለች። ከዚያ ስትመለስ፥ ለሚጠብቃት የሥራ ጎላፊነት፥ የመንፈስ ስንቋን ሰንቃ፣ ብርታት አግኝታ ትመጣለች። ወደ በረኻ ስትሄድ፥ ተራ የሚደርሳቸው ሦስት መነኲሳይያት አብረዋት ይሄዳሉ።

ከምትሄድባቸው በረኻዎች አንዱ፥ እስክንድርያ የሚገኘው «ኪንግ መርዩጥ» የሚባለው ነው። በየዓመቱ ወደዚያ ስትሄድ፤ ከድካሟ ታድሳ ብቻ ሳይሆን፥ ለወደፊቱም ጎይል አግኝታ መምጣቷ፤ ከከተማ ውጪ ጸጥታ በተሞላ ሥፍራ ገዳም ለመመሥረት ካነሣሧት ምክንያቶች አንዱና ዋናው ነው። እርሷ እንደምታደርገው ሁሉ፤ እያንዳንዷ መነኲሲት ይህን ዕድል እንድታገኝ ጽኑ ምኞት ነበራት። ይህ ዐላማዋ በቀላሉ እንደማይፈጸም የታወቀ ከመሆኑም በላይ፥ በተለይ ደግሞ በሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች ጥያቄዋ አደገኛም ነበር። ይኸውም፦

፩ኛ) ማንኛውም ገዳም ባለበት ተወስኖ አገልግሎት መስጠት እንጂ፤ ሌላ ቦታ ላይ ሌላ ገዳም መመሥረት የሚያስችል ሥልጣን ስለሌለው፤

፪ኛ) ገዳማዊ ሥርዓቱ ራሱ፤ አንዲት መነኲሲት፦ እንኳን በማንኛውም የመንግሥት ቢሮ መገኘት፣ ከሚንስትሮች ጋር መገናኘት፣ ምንም ዐይነት ከመረጃዎች ጋር የተያያዘ ውል መስማማትና መፈረም፤ ምንም ዐይነት መንግሥታዊም ሆነ ሌላ ድርጅታዊ ጉዳይ መፈጸም ይቅርና፥ ከበኣቷ ወጥታ ወደ የትም መሄድ እንደማይፈቅድ ጣማፍ ራሷ በደንብ ታውቃለች።

፫ኛ) ፈቃዱ ቢገኝ እንኳን፤ ወደዚያ ተመላልሳ የማንባታ ሥራ ለማሠራት ልምዱ ስለ ሌላት፤ ሌሎች ችግሮች ይዞ ይመጣል።

ከነዚህ ከሦስቱ ሌላ፥ መሠረታዊ ችግሮችም ነበሩ። ገዳሙን የመሥራት ጎላፊ ነት ከተቀበለችበት ጊዜ ጀምሮ፤ ገዳሙ ከፍተኛ የገንዘብ ችግር ነበረበት። እርሷ ግን፥ የገዳሙን መንፈሳዊ አገልግሎትና ዕድገት፤ ምንም ዐይነት ምክንያት እንዲያቆመው የምትፈቅድ ሴት አይደለችም። የመጣው ቢመጣ፥ ዐላማዋ የማይናወጥ፤ እምነቷ የማይናጋና ራእይዋን እውን ሆኖ ለማየት ጽኑ ፍላጎት ያላት በመሆኗ፤ ለዚህ ዐይነቱ አገልግሎት ፈር ቀዳጅ (ፋና ወጊ) መነኵሲት ለመሆን በቅታለች። ለዚህ ተጋድሎዋ፥ እኛ ገዳማውያኑም የዓይን ምስክሮች ነን። መመሪያዋ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «እኔ ግን እጥፍ ድርብ አወጣለሁ፤ ስለ ሰውነታችሁም ነፍሴን አሳልፌ እሰጣለሁ፤ እናንተንም እጅግ ብወዳችሁ ራሴን ወደድሁ» (፪ኛ ቆሮ.፲፪፥፲፭) የሚለው መልእክት ነው።

የውስጧን መቃጠልና ለቤቱ ያላትን ቅናት እግዚአብሔር ያያልና፥ ቤቱን ታሰ ፋለት ዘንድ ፈቃዱ ስለሆነ፤ አባቷ ቃዋጋ ያሳ ኬላ በታኅሣስ ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. ሲያርፍ በውርስ ያገኘችውን[11] ገንዘብ፤ እስከ ፲፱፷፫ ዓ.ም. ድረስ ለልዩ የግንባታ ሥራዎች አውላ ጨረሰችው። ከ፲፱፷፬ዎቹ ማለቂያ ጀምሮ ባሉት ዘመናት፤ ገዳማችን ሰፊና ታዋቂነቱም የገነነ ሆነ። ይህን ማየታችን፥ በእግዚአብሔር ላይ ያላትን ጽኑ እምነትና መንፈሳዊ ጥንካሬዋን ለመመስከር አብቅቶናል። እውነተኛ ግብኣቷም እግዚአብሔር ብቻ ነበር። ሁሉን ቻይ በሆኑ እጆቹ ትታመናለች፤ ስሙን ትጠራለች። እርሱም በጎ ያላን እጆቹ ሥራዋን ይባርክላታል። ተኣምራትንም ይፈጽምላታል።

በበረኻ፥ ገዳም ለመመሥረት ያሰበች ጊዜ፤ ገዳማውያኑ በየግል ጸሎታችን ፈቃደ እግዚአብሔርን አጥብቀን እንጠይቅ ዘንድ አሳሰበችን። እንዲሁም በኣንድነት የሚጸለየውን የሦስተኛው ሰዓት የጸሎት ጊዜም፤ ለዚሁ ዐላማ እንዲውል ነገረችን። ለምን ይህን ሰዓት እንደ መረጠች ስንጠይቃት «ለሁለት ምክንያት ነው። ይኸውም ፩ኛ) በኣያንዳንዷ እርምጃችን መንፈስ ቅዱስ ይመራን ዘንድ። ፪ኛ) የሰዓቱ ጸሎት "በመከራህ ጊዜ እግዚአብሔርን ጥራ" ብሎ ይጀምራልና ነው» አለችን። በባሕርይው ምስጉን የሆነ እግዚአብሔርም፤ የጸሎታችንን ዋጋ ከፈለን። ክቡር ስሙ የሚወደስበትንና የሚቀደስበትን ሥፍራ መርጦ ሰጠን።

<u>ሰሜናዊው የባሕር ዳርቻ</u>፦ «ያቤጽም አባክህ መባረክን ባርከኝ፥ ሀገሬንም አስፋው፤ እጅህም ከእኔ ጋር ትሁን፤ እንዳያሳዝነኝም ክክፋት ጠብቀኝ ብሎ የእስራኤልን አምላክ ጠራ፤ እግዚአብሔርም የለመነውን ሰጠው» (፩ኛ ዜና.፬፥፲)። ጣማፍ ስለ ገዛችው መሬት፤ በሂደቱ ስለ ተፈጠሩ ትና ስለ ተከናወኑት ሁኔታዎች፤ ከእስክንድርያ በስተ ምዕራብ የሚገኘው ሰሜናዊ የባሕር ዳርቻ፥ ሕያው ምስክር ነው። ግዢው የተፈጸመው፤ እግዚአብሔር በዕድሜ በጤና ይጠብቅልንና፤ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኑዳ ፫ኛ የፓትርያርክነት ምርጫ ጊዜ ነበር። ጣማፍ በ፬/፫/፳፬ና ፮/፱/፱፯፥ መሬቱን በሕጋዊ በባለቤትነት አስመዝግባዋለች።

[11] ወላጆቿ የሃብታምና ታዋቂ ቤተሰብ ልጆች እንደ መሆናቸው፥ እጅግ ብዙ ገንዘብና መሬት በውርስ አግኝታ ነበር። ያገኘችውን ገንዘብ በሙሉ ለገዳሙ ማስፋፊያ አውላዋለች።

በዚህ ሁኔታ ገዳማችን፤ በሰሜናዊው የባሕር ዳርቻ፤ ሲዲ-ክሬይር (Sidi-Krair) በተባለ ቦታ ላይ፤ ሃምሳ ሁለት አክር[12] (acres) አካባቢ የሚሆን መሬት ባለ ይዞታ ሆነ።

እናት ኄራኒ በእግዚአብሔር መሪነት፤ ሲዲ-ክሬይር በረኻ ላይ፤ ይህን መሬት ለማግኘት ለ፴፩ ዓመታት ለፍታለች። ሆኖም ግን በቦታው በተደረጉ ድንቅ ተኣምራት ምክንያት፤ ቦታውን ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ በያዙት የኣካባቢው ዘላኖችም ሆነ በመንግሥት ሠራተኞች ዘንድ፤ የእግዚአብሔር ስም ተመስግኖበታል። ጥበበ እግዚአብሔር በኣስቸጋሪ ሂደቶች ውስጥ ሁሉ፥ እንዴት ይረዳንና መንገዳችንን ያቀናልን እንደ ነበረና፥ እንዲሁም ከተሠሩት ተኣምራት ጥቂቱን እነሆ፦

<u>እግዚአብሔር የመረጠው ሥፍራ</u>፦ *በኪንግ መርዩጥ በረኻ በሚገኘው የኣቶ ኤክስ ሕንፃ ላይ፤ የዕረፍት ጊዜ እያሳለፍሁ ነበር። ያን ጊዜ አካባቢው ጭው ያለ በረኻ ነበር። በውስጤ እንደዚህ ጸጥ ያለ ቦታ ብናገኝና፤ ለካይሮው ገዳማችን ልጅ የምትሆነንን ገዳም፤ መመ ሥረት ብንችል እያልሁ በጣም ተመኘሁ። ስለዚህ ኣቶ ኤክስንና፤ በእስክንድርያ ኣል -ሐዳራ የቅ.ጊ.ቤ.ክ. ሰባኬ ወንጌል የሆነውን ኣባ ተክላ ላቢብን፤ ካይሮ ያለው የሴቶች ገዳም በሰው መጨናነቁን ገልጬ፤ የሚሸጥ መሬት እንዲያገኙልኝ ጠየቅኋቸው።*

ከጥቂት ቀናት በኋላ፥ ኣባ ተክላና ባለቤቱ ዶ.ር ፋይዛ ኣዚዝ ሻላቢ፤ እኔን ለመጠየቅ ወደ ካይሮ ገዳም መጡ። የደረሱትም በሦስተኛው ሰዓት የጸሎት ጊዜ ነበር። እንዳገኙኝ፥ «እማሆይ! እኔ ከኣቶ ኤክስና ኣንዲት የእስክንድርያ ዶክተር ጋር ሆኜ፤ ሲዲ-ክሬይር ላይ መሬት ገዝቼ ነበር። የገዛሁበት ዐላማ፥ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የበጋ ጊዜ ኣገልግሎት እንዲሰጥ ቢሆንም፤ ባለቤቴ ግን፥ ለሦስት ተከታታይ ቀናት፤ ተመሳሳይ ሕልም ስላየች ልናናግርሽ መጣን» ኣለች።

የኣባ ተክላ ባለቤትም ሕልሟን እንዲህ ስትል ነገረችኝ። «ልክ ኣንደ ሊቃነ መላ ኣክቱ በብርሃን የተከበበ ኣንድ ሰው፤ በሥፍራው ቆሞ ኣየሁ። ሰውየው ይህ ቦታ ለመዝናኛ የሚሆን ኣይደለም፤ ገዳም ነው ኣለኝ። ይህን ሕልም ለባለቤቴ ስነግረው፤ በቀን ያሰብሽው ነው በሕልምሽ የመጣው ኣለች። እኔ ግን ለሁለተኛና ሦስተኛ ጊዜ ደጋግሜ፤ ያንኑ ሕልም ኣየሁ። በሦስተኛው ሕልሜ ላይ፤ ሰውየው እርሱው ሆኖ፥ ጢሙ፤ ጠጉሩና ልብሱ ግን ነጭ ነው። ትልቅ ብርሃናዊ ምልክት የያዘ ሲሆን፥ ላዩ ላይ «የኣቡ ሳይፊን የሴቶች ገዳም» የሚል ማስታወቂያ ተጽፎበታል። የኣንቺ ያልሆነውን መሬት እንዴት ትወስጃለች? ብሎ ሲቆጣኝ፤ ወዲያው ነጫጭ ርግቦች በመሬቱ ላይ ረበው ሲበሩ ኣየሁ። ሰውየው «ለኣባ ተክላ ይህ የኣንተ ቦታ ኣይደለም በይው» ኣለኝ።

እኔም ሕልሟን ካደመጥሁ በኋላ፥ «ለመሆኑ ኣሁን መነኵሳይያቱ በላይኛው ክፍል ውስጥ ተሰብስበው፤ እግዚአብሔር መፍትሔ ይሰጣቸው ዘንድ እየጸለዩ መሆ

[12] ኣንድ acres ኣራት ሺህ ኣርባ ስድስት ነጥብ ሰማንያ ስድስት ሜትር ስኴር ነው (1 acres=4,046.86 m²)።

ኑን ታውቂያለሽን? አሁን እናንተ ያመጣችሁልኝ ዜና፤ የጸሎታችን መልስ ነው። እግዚአብሔር ቦታውን ለእኛ ፈቅዶታልና» ስላቸው፤ አባ ተክላ «እባክሽ እማሆይ፤ ነይና ቦታውን አይተሽ ተረከቢን» አለች። ሄደ ቦታውን ሳየው፥ ውስጤን ይህ ነው የማይባል ደስታና ሰላም ተሰማኝ። ልክ እንደ ጥንታዊው የአባ አንጦንስ ገዳም፥ የተባረከ ቦታ ነው። በደስታና በተመስጦ እነዚህ ወዳጆቼ አንዴ ካሰረከቡኝ በኋላ፥ ቦታችንን መልሱልን ቢሉኝ እንኳን፤ እንደማልለቅላቸው እያሰብሁና እየጸለይሁ ነበር። ሁላችንም በአንድነት ሆነን ስንጸልይ፤ ሦስት ነጫጭ ርግቦች፥ ዙሪያችንን ዞረው፥ ከበላያችን አልፈው ሄዱ። ከእነርሱ በኋላ ደግሞ፥ መዓዛው ደስ የሚያሰኝ የዕጣን ሽታ አካባቢውን አወደው። የሆነው ነገር ሁላችንንም አስደምሟል። አባ ተክላም ዕንባውን እያፈሰሰ በተአምሩ መደሰቱን ነገረኝ።

እኔም «እንግዲህ አባቴ! መሬቱን ለመውሰድ ፈቃደኛ ነኝ። ነገር ግን፥ አሁን በእጅ ላይ ምንም ገንዘብ የለኝም። ለመሆኑ ሰንት ነው የከፈሉበት?» አልሁት። ዶር ዋይ (የእስክንድርያዋ ዶክተር) ወደ ውጭ ሀገር ስለምትሄድ፤ ድርሻዋን አስቀድመሽ ክፈያት። እኔና አቶ ኤክሰ ግን፥ ገንዘብ አስከምታገኚ ድረስ መታገስ እንችላለን አለች።

ቦታው ምንም ሕንፃ የሌለውና ሰፋቱ ሰድስት አክር ነው። አቶ ኤፍ በሚባል፥ በአንድ ወዳጃችን እርዳታ፤ ለመነኮሳይያቱ በኣት የሚሆን አነስተኛ ሕንፃ ገነባን። በዚያው ሰሞን ደግሞ፥ በአውራ ጎዳናው ትይዩ ያለና ሰፋቱ አራት አክር የሆነ፤ የዚህ መሬት አዋሳኝ፤ ለሽያጭ መቅረቡን ሰማን። በግዢው በኩል እግዚአብሔር ይረዳን ዘንድ ሰንጠብቅ፤ በሰሙነ ሕማማት እሑድ፥ የሕግ አማካሪያችን ስልክ ደውሎ፤ የአካባቢው ባለሥልጣንና የቦታው ባለቤት የሆነው ሰው፥ መሬቱን ሊሸጥላችሁ ተሰማምቷልና ምን ትላላችሁ? ሲል ጠየቀኝ። ባለ መሬቱ ዋጋውን ቢያስወድድብንም፤ እግዚአብሔር የቸርነት እጁን ዘርግቶልን ቦታውን ለመግዛት ቻልን። ፈቃደ እግዚአብሔር ሆኖ፥ በኣል-ጋባላያ (Al-gabalaia) የሚገኝ ዳገታማ ቦታ ላይም እጅግ ሰፊ መሬት ገዛን። የግዢ ሂደቱ አሰቸጋሪ ቢሆንም፤ የእግዚአብሔር እጅ ሁሉን አስተካከለው።

«አምላካችን መጠጊያችንና ኀይላችን፥ ባገኘን በታላቅ መከራም ረዳታችን ነው። . . . የሠራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው፤ የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው» (መዝ.፵፮፥፩ ፤ ፶፩)። በግዢው ውጣ ውረድ ሂደት፤ ጣማፍ ብዙ መሰናክሎች ስለ ገጠሟት፤ ምሕላ ለመያዝ ተጨማሪ የጸሎት ሰዓት አስፈላጊ ሆነ። እግዚአብሔር የቸርነቱን ሥራ ይሠራልን ዘንድ፤ ማኅበረ መነኮሳቱ ከዓብይ ጾም በፊት፥ በየዕለቱ፤ መጸለይ ነበረብን። ሱባኤው ሲያልቅ፤ አቡ ሰይፊን የብርሃን መስቀል ይዞ ለጣማፍ ተገለጠላት። ኽሬይር በሚገኘው መሬት ላይ እየተዘዋወረ ነበር ያየችው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ ደግሞ፥ በጣዕውጎ ይዞ ከኋላው አለ። አቡ ሰይፊን በመጀመሪያ በመስቀል አካባቢውን ባረከና፤ አቡነ ቄርሎስ ጠበሉን እንዲረጭ ነገረው። በዚህ ሁኔታም እያንዳንዷን ቁራጭ መሬት በአንድነት ሆነው ባረኩ።

ከዚህ ሕልም በኋላ፤ ጣማፍ የተወሰኑ የመገልገያ ቍሶች፤ ወደ አዲሱ ገዳም እንዲወሰዱና አገልግሎት እንዲጀመር አደረገች። ይህ የመጀመሪያ እንቅስቃሴ የተደረገው፤ ማክሰኞ ዕለት ግንቦት (Bashans) ፲፬ ቀን በ፲፱፻፩ ዓ.ም. ሲሆን፤ ዕለቱ የአንድ ነት ኑሮ መሥራቹ፥ የታላቁ አባት የቅዱስ ጳኩሚየስ፤ በዓለ ዕረፍት የሚዘከርበት ነው። የዕለቶቹ መገጣጠም፤ ለእኛም ሆነ ለእናታችን ኄራኒ ልዩ የበረከት ምልክት በመሆኑ፥ ደስታችን ታላቅ ነበር። አቡ ሰይፊን በተደጋጋሚ፥ ለእናት ኄራኒ እየተገለጠ «ይሄንን መሬት እግዚአብሔር ለእናንተ መርጦታል፤ እኔም እንዲሁ። ስለዚህ ምንም የምትፈሪው ጉዳይ አይኑር። ድካሙና መሰናክሉ የበዛ ቢሆንም፤ አንቺን የሚያጠነክ ርና፤ በቦታው ላይም ተደላድለሽ እንድትቆሚ የሚያደርግሽ ነው» ይላት ነበር።

በእርግጥም በእያንዳንዱ መሰናክልና የሰይጣን ፈተና፤ ከሃሌ ሉሉ የሆነ ፈጣሪአችን ይደርስና ይረዳን ነበር። ለምሳሌ ያህል ሁለቱን ልንገራችሁ፦ «እኔ አድንህ ዘንድ ከእንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ፥ ይላል እግዚአብሔር» (ሔር.፩፥፰)። በደቡባማው ክፍል ያለው የመሬት ባለቤትና በጥበቃነት የቀጠረው ዘላን፤ በብዙ ነገሮች ችግር አየ ፈጠረ ይፈታተነኝ ነበር። አንድ ጊዜ እጅግ ብዙ ገንዘብ እንድከፍለው ጠየቀኝ። ሌሊቱን ወደ እግዚአብሔር ሰጸልይ አደርሁ። ለሰማዕቱም «ይህ መሬት የአንተ ነውና፥ አንድ መፍትሔ ስጠን» ብዬ በጸሎት አሳሰብሁ። በማግሥቱ ጠዋት፥ ዘላኑ ወደ ሕግ አማካሪአችን ጽሕፈት ቤት ሄዶ፤ ይቅርታ ጠየቀውና፥ «ግንባርህን ልሳም!» አለው። ሁኔታው ግራ ያጋባው ሕግ አማካሪ፤ የተፈጠረውን ነገር ንገረኝ አለው። እርሱም «ያንን ሁለት ሰይፎች የሚይዝ ሰውዬ ላስደሰተው አፈልጋለሁ። ማታ ወደ መኝታዬ እንደሄድሁ፤ ሁለት ሰይፎች የያዘ ወታደር መጥቶ፥ "ተነሥ" አለኝ። እኔም "እሺ ጌታዬ" ብዬ ብድግ አልሁና፤ ለወታደር የሚገባውን የአክብሮት ሰላምታ ሰጠሁት»።

«ማን እንደሆንሁ ታውቃለህን? ብሎ ሲጠይቀኝ፥ «አላውቅምትም ጌታዬ!» አልሁት። «እኔ አቡ ሰይፊን እባላለሁ»፤ የዚህ መሬት ባለቤትና የመነኮሳይያቱ አባት (ጠባቂአቸው) ነኝ» አለኝ። ቀጠለና፥ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሲል የተቀበለውን መከራና በሰማዕትነት ክብር ማለፉን፤ አንድ በአንድ ታሪኩን፥ የሁለተኛውን ሰይፍ ታሪክም ጨምሮ ነገረኝ። በመጨረሻም «ትእዛዜን ብትሰማና ብትፈጽመው፤ በነገሮች ሁሉ እረዳሃለሁ፤ ሀብታምም ትሆናለህ። ከትእዛዜ ከወጣህና በልጆቼ ላይ በደል ከፈጸምህ ግን፤ መከራህን አበዛዋለሁ» አለኝ። እኔም «ይቅር በለኝ! በማንም ላይ ጉዳት ላለማድረስ ቃል እገባለሁ» ስለው፤ ወዲያው ተሰወረ። ከዚህ በኋላ ዕንቅልፍ ሊወስደኝ አልቻለም። ነግቶ ወደዚህ መጥቼ ይቅርታ እስከምጠይቅ ቸኩዬ ነበር» አለው። ከዚህ ዕለት ጀምሮ፤ ከዘላኑ ትንኩሳ ተገላገልን። አንዳንድ ጊዜ ሊያስቸግር ሲመክር፥ ባለ ሁለት ሰይፉን ሰማዕት እናስታውሰዋለን። እርሱም ያርፋል።

ሁለተኛው ተአምር ደግሞ፤ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ስለ ነበረው ዘላን ነው።

አንድ ቀን ቦታውን ለማየት ወደዚያ ስሄድ፤ በቦታው የጥበቃ ተረኛ የነበረችው መነኵሲት፤ በሰሜን ያለው ዘላን በጣም ሲፈልግሽ ነበር ስላለችኝ፥ ወደ እንግዳ መቀበያ አስገቢውና ሻይ ጋብዢው አልኋት። እኔን ሲያየኝም፤ «እጅግ በጣም ብዙ የሆነ ገንዘብ ያስፈልገናል» አለኝ። እኔም ይህን ያህል ገንዘብ ከየት አምጥተን ነው የምንሰጥህ? እኛኮ ድሆችና የተሟላ ኑሮ የሌለን፤ በጭንቅ የምንኖር ማኅበር ነን አልሁት።

በስጨት ብሎ ከተቀመጠበት ተነሣና፤ ከኪሱ ትልቅ ሴንጢ አወጣ። እጁን ወደ እኔ ሰንዝሮ «ወይ ብሩን ታመጫለሽ! ወይ ጉዳት ይደርስብሻል!» አለኝ። እኔም እየሳቅሁ «አይ! አልከፍልህም። ልትገድለኝ ከፈለግህም ይኸው! አጠገብህ ነኝ» አልሁት። እጁ እንደተሰነዘረ ቢሆንም፤ ማንቀሳቀስ ተሳነው። እኔም «ምን ትጠብቃለህ? ይኸው እዚሁ ነኝ፤ አልፈራህምም» አልሁት። ሴንጢው ከእጁ አምልጦ ወደቀበት። እጁም ባለበት ሽባ ሆኖ ቀረ። መጮኽ ሲጀምር ብድግ ብዬ፥ «ምን ሆነኻል?» ስለው «እባክሽ እርጂኝ፤ እጀን ማንቀሳቀስ አልቻልሁም። ሕመሙንም አልቋቋመውም» አለኝ። እኔም በሕሊናዬ ለእግዚአብሔር ከሙሉ ልብ የመነጨ ምስጋና አቀረብሁ። እርሱንም አትፍራ እግዚአብሔር ይምርሐል። ሆኖም አሁን ልትፈጽመው የነበረውን ነገር ዳግም እንዳታስበው! አልሁት። ከእንግዲህ በፍጹም እንደማይምክረው ፈጥኖ ቃል ገባልኝ። ከመዝሙረ ዳዊት «በመከራ ጊዜ ጠራሽኝ፥ አዳንሁህም» የሚለውን ቃል ደገምሁና፥ በእጁ ላይ በትእምርተ መስቀል አማተብሁበት፤ እጁም መንቀሳቀስ ቻለ።

«እባክሽ በእኔ አትዘኚ! ሰዎች ናቸው ይህን እንድፈጽም የላኩኝ። እንዳስፈራራሽና ደንግጠሽ ቦታውን ጥለሽ እንድትጠፊ ለማድረግ ነበር የታሰበው። አሁን ግን እግዚአብሔር ከላንቺ ጋር መሆኑን ተረድቻለሁ። ከእንግዲህ ምንም ዐይነት መጥፎ ሙከራ አላደርግምና፤ እባክሽ አትዘኚብኝ!» ብሎ ተማጸነኝ። አላዘንሁብህም፥ ነገር ግን፤ ከእንግዲህ በፍጹም እንደዚህ እንዳታደርግ። በእኔ ላይ ምንም ቢደርስብኝ፤ ሰማዕትነት ነውና አያስጨንቀኝም። ያሳሰበኝ ግን፥ አንተ ስለ ፈጸምኸው በደል የምታገኘው ቅጣት ነበር፥ አልሁት።

ጣማፍ ኄራኒ፥ ከበሽታዎቿ በተጨማሪ፤ ይህን የመሰለውን የጠላት ማነፍነፍ ፈተና፤ በእግዚአብሔር ጎይል እየተቋቋመች ነበር፥ ለብዙ ዘመናት እየተጋደለችና እያገለገለች የኖረችው። ፈተናዎቹ የሚመጡት፥ በማንኛውም እንቅስቃሴዋ፤ በብሕትውና ሕይወቷ፤ በጸሎትና በጾሟ፤ . . . በሁሉም ዘርፍ ነበር። የገድልዋን ዋጋ እግዚአብሔር ወዲያው ስለሚከፍላት፤ ከዓላማዎቿ ሁሉ፥ ጀምራ ሳታሳካ ወይም ሳትፈጽም የተወችው የለም። ይህንን ኽሬይር የሚገኘውን ገዳማችንን ለመጨረሻ ጊዜ ስት ጎበኝ፤ የድካሟን ውጤት አይታና በፍሬው ተደስታ፤ በረከተ እግዚአብሔር በቦታው ላይ መሆኑን፤ እርግጠኛ ሆና ነው የተመለሰችው። በዚህ የመጨረሻ ጉብኝት ያገኘችው ደስታ፤ የገድሏ ፍጻሜ ለመሆኑም ምልክት ሆኗታል።

በረኸም የመከራና የተጋድሎ ውጤት ያቆመችልን ይህ ገዳም፤ ከእርሷ ያገኘነው ገጸ በረከት ነው። ከራእዮቿ በአንዱ፥ ወላዲተ አምላክ ተገልጣላት «የምወደው ልጄ በረከት ከአንቺ ጋር ነውና፤ ሁሌም ውጤታማ! ውጤታማ! ውጤታማ! . . . ትሆኖለሽ» ያለቻት ትንቢትም እውን ሆኖ ታየ። በእግዚአብሔር ቸርነትና ረድኤት፤ ኽሬይር የሚገኘው ገዳም፤ ማር እንደሚቆረጥበት የንብ ቀፎ ነበር የሆነው። ይህ ደግሞ የተደራጀና የሰላማዊ አሠራር ሥልቷ ምስክር ሆኖ ይኖራል። እያንዳንዱ ጥቃቅን የሥራ ውጤትም የሚያሳየው፤ በረከተ እግዚአብሔር፤ የአመቤታችን አማላጅነትና የቅዱሳኑ ተራዳኢነት፤ ምን ያህል አብሮን እንዳለ ነው። ሁሌም የደስታችንና የመረጋጋታችን ምንጮች፤ የእግዚአብሔር ቅዱሳን ናቸው። ጥበቡን በቸርነቱ ለግሷት፤ እነዚህን ተግባራት እንድትፈጽም የረዳትን እግዚአብሔርን ዛሬም ዘወትርም ለዘለዓለም እናመሰግነዋለን! አሜን።

የአዲሱ ገዳም ባለ ሦስት ፎቅ ሕንፃ፤ የ«ዘ» ቅርፅ ያለው ሲሆን፥ የታነፀው ተራራማው ቦታ ላይ ነው። በስተ ሰሜን በኩል፥ ለባሕሩ ትይዩ ሲሆን፤ በስተ ደቡብ ደግሞ ለማላሃት (Malahat) ትይዩ የሆነና የ«L» ቅርፅ ያለው፤ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል ሕንፃ ተገንብቷል። በመካከል ደረጃቸውን የጠበቁ እጅግ ውብ አበቦች የተተከሉበት ዐጸድ አለው። ሁሉም የእግዚአብሔር ስም ይመሰገን ዘንድ ተደረገ።

የሕንፃው የመሠረት ድንጋይ የተቀመጠው፤ በዕለተ እሑድ ሕዳር ፲፫ ቀን ፲፱፻፭ ዓ.ም.፤ በክብርት እናታችን እጆች ነው። የመሠረት ድንጋዩ ሲቀመጥ፥ ከሥሩ መዝሙረ ዳዊትና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፤ የብረት መስቀል፤ የደረቀ ጎብስት[13]፤ ሳንቲም እና የጊዜውንና የቦታውን ታሪክ የሚገልጽ (ቦታው እንዴትና ከማን እንደ ተገዛ፤ ሕንፃው እንዴት እንደ ታነፀ በዝርዝር የተጻፈበት) ቅጽ፤ የወቅቱ ርዕሰ ቤተ ክርስቲያን የብፁዕነታቸው አቡነ ሲኑዳ ፫ኛና የሃገሪቱ መሪ የፕሬዚደንት ሆስኒ ሙባረክ ስም፤ የተጻፈበት መዝገብ በሣጥን ተደርገው ከተቀመጡ በኋላ ነው።[14] የቅጹ ግልባጭ ደግሞ፤ በገዳሙ ቤተ መጻሕፍት ተቀምጧል።

በገዳሙ ውስጥ ያሉን ንብረቶች፦

፩) ራሱን የቻለ መጸዳጃ ክፍል ያለው የእንግዳ መቀበያ አዳራሽና፥ የገዳሙ የሥራ ውጤቶች፥ ለገበያ የሚቀርቡትን ዕቃ የያዘ ሕንፃ፤

፪) ወይን፤ ሾላ፤ የወይራ ፍሬና ተምር የሚመረትበት የእርሻ ቦታ፤

፫) የወይራ ፍሬ መፍጫና መጭመቂያ፤ ኮምጣጣ (pikl) (ሙኽለል) የወይራ ፍሬ ማዘጋጃና ፍራፍሬዎች ማድረቂያ መሣሪያዎችን የያዘ ሕንፃ፤

[13] {እነርሱ ቍርባና የሚሉት የቡራኬ ዳቦ።}
[14] {ታሪክን ለዘመናት ለማሸጋገር ይረዳ ዘንድ።}

፬) የከብት እርባታ፥ ከተሟላ የወተት ማለቢያ፣ እርጎ ማዘጋጃ፣ መናጫና ዐይብ ማዘጋጃ መሣሪያ ጋር፣

፭) ለርግብና ጥንቸል ማርቢያ የተለየ ሥፍራ፣

፮) የእርሻ መኪናና ሌሎች ማሽኖችን መጠገኛ (ጋራዥ)፣

፯) የዕንጨት ሥራ ማከናወኛ፣

፰) የጀነሬተር ማስቀመጫ ሕንፃ፣

፱) አራት ዋና በሮች ያሉትና፥ ከፍታው አምስት ሜትር የሆነ የግንብ አጥር፣

፲) በየአቅጣጫው የተዘጋጁ፣ ተፈጥሮን ለማድነቅ፣ በተመስጦ በተረጋጋ መንፈስ ለጸሎት የሚጋብዙ፥ የኣትክልት ሥፍራዎች፥ አሉ።

ገዳሙ የጎበኙትን ሰዎች ሁሉ ቀልብ የሚስብ ሲሆን፣ «የኢ.ሰ.ሴ.ገ. የሕንፃ ግንባታ ጥበብ፣ የቅብጥ ገዳማትን ገጽታ የቀየረ መሆኑን ታሪክ ሲያወሳው የሚኖር ነው። በኣሮጌዋ ካይሮና በሲዲ-ክሬይር ያሉትን እናትና ልጅ ገዳማት የተመለከተ ሁሉ፣ የቅብጥ ገዳማትን እንዲያወድስ ምክንያት ይሆነዋል» ሲል አንድ ተሳላሚ ተናግሯል። ይህ የሥራ ውጤት፥ ጥበበ እግዚአብሔር የሚገለጥበት፣ ገዳሙ በስማቸው የተሰየመላቸው ቅዱሳን ተራዳኢነት፣ እንደ እማሆይ ኄራኒ ያሉ አገልጋዮች ትጋትና ጥንካሬም የሚታይበትና የሚነገርበት ነው። በተለይ የእነዚህ ሁለት ገዳማት ግንባታም ሆነ የውስጥ አደረጃጀት፣ የሥነ ውበት አጠባበቅና እያንዳንዷ ቁራጭ መሬት የያዘችው፣ መስሕብ የሆነ የጥበብ ውጤት፣ የእናት ኄራኒን ልዩ የኣገልግሎት ፍቅር የሚያሳይ ነው። ፍቅሯን የገለጠችው በጠንካራ ሥራ፣ በንቃትና በጽኑ ጸሎት እየታገዘች፣ ምድረ በዳውን ወደ አምላለ ገነትነት በመለወጥ ነው። እንዲሁም፥ በሥራዋ ሁሉ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ ፫ኛ፣ ድጋፍና ጸሎትም አልተለያትም።

«የግዞት ቤቱም አለቃ በእጁ ያለውን ነገር ከቶ አላስበም፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበርና፥ የሚያደርገውንም ሁሉ እግዚአብሔር ያቀናለት ነበር» (ዘፍ.፴፱፥፪፫)፣ «እኔ ራሴ ተናግሬአለሁ እኔ ጠርቼዋለሁ፣ አምጥቼዋለሁ መንገዱም ትከናወንለታለች» (ኢሳ.፵፰፥፲፭)። እንዲል ቃለ እግዚአብሔር።

ቡሩክና ታሪካዊ ጉብኝት።

እግዚአብሔር ረጅም ዕድሜና ጤና ይስጥልንና፣ ብፁዕ አባታችን ክሬይር የሚገኘውን የሴቶች ገዳም ብዙ ጊዜ ጎብኝቶታል። በእናት ኄራኒ ልብም ልዩ ሥፍራ ያለው አባት ነው። እርሱ ወደ ገዳሙ በሚመጣባቸው ጊዜያት ሁሉ፣ በእያንዳንዱ ዝግጅት እርግጠኛ ለመሆን ካላት ፍላጎት የተነሣ፣ አስፈላጊ ነገሮችን እርሷ ራሷ ትፈጽማለች እንጂ፥ ለሌሎች ጎላፊነቱን አትሰጥም። በእነዚህ ጊዜያት፥ ሕመሟንም ቢሆን ደብቃ ማንም እንዳያውቅባት ለማድረግ ትጥራለች፣ ከሁሉም ቀድማ ቡራኬውን ለመቀበል ትፈጥናለች። በእርሱና በሌሎች ጳጳሳት የጉብኝት ጊዜ፥ እኛም ታላቅ ደስታ ይሰማናል።

አብረን በምናሳልፈው ጊዜ፥ በሚደረግ መንፈሳዊ ውይይት፣ ችግራችንና ሸክማችን ይቀል ልናል። ከጉብኝቶቹ ሁሉ ዋናዎቹን ለመጥቀስ ያህል፣ የሚከተሉትን እንይ፦

፩) በ፳፫/፭/፳፫ የሕንፃው ግንባታ እንደተጠናቀቀ መጥቶ ነበር። በዚህ ጉብኝቱ፥ መነ ኩሳይያቱ አደጋ እንዳይገጥማቸው፣ ዐጥሩና በሩ በጥሩ ሁኔታ እንዲሠራ መመሪያ ሰጥቷል።

፪) በ፳፬/፯/፳፬ በመጣ ጊዜ፣ በጊቢው ውስጥ ጥቂት ዛፎችን ተክለ።

፫) በግንቦት ፲፱፻፫፭ ዓ.ም.፥ ከብዙ ብፁዓን ሊ.ጳ. ጋር ታሪካዊ ጉብኝት አደረገ።

፬) በሚያዝያ ፲፱፻፹ ዓ.ም. የማጠናቀቂያ የግንባታ ሥራዎችን ለማየት መጣ።

፭) በ፳፩/፲፱/፺ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተገኝቶ፣ ጸሎት አድርሶና፥ ጊቢውን በሙሉ ጎብኝቶ፣ መነኮሳይያቱን ሰብስቦ ለጥያቄዎቻቸው መልስ ሲሰጥ ዋለ። እናት ኄራኒ፥ ዳገታማ ቦታ ላይ ያለውን የገዳሙን ይዞታ ካሳየችው በኋላ፣ ለበኣት የሚሆን ትልቅ ሕንፃ ይታነፅበት ዘንድ ጠየቀች። (የእርሱን ይሁንታ ስታገኝ፣ በጎዳር ፲፱፻፺፯ ዓ.ም. የግንባታ ሥራው ተጀመረ)። ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን፥ የጉብኝት ውሎውን በዚህ ሁኔታ ካጠናቀቀ በኋላ፣ ቀለል ያለ ማዕድ ተዘጋጅቶ፥ ከሕንፃው ፊት ለፊት በሚገኘው ዐፀድ ውስጥ በኣንድነት ተመገብን።

፮) ከዚያም በኣሮጌዋ ካይሮ የሚገኘውን «እናት» ገዳማችንን ረቡዕ ዕለት ፳፩/፫/፺፰ ጎበኘ። እናት ኄራኒ፥ ወንድሟ መሓንዲስ ኢዛት ያሳ አርፎ ስለ ነበር፣ የማጽናኛ ምክር ሰጣት። እርሷም ወደ ሁለተኛው ገዳማችን መጥቶ ይጎበኝ ዘንድ አሺታውን ተቀበለች። የሚመጣበት ጊዜ ሲደርስ፣ ከሕመመ ሥጋዋ በላይ የሆነው ልቧ፥ የፈቀደላትን ያህል ተገቢውን ሁሉ አሟልታ ልትቀበለው ብትዘጋጅም፣ የማይቀረው ሞት ቀድሟት፥ ልታስተናግደው አልቻለችም። ወደ ዘለዓለማዊ አባቷ ዘንድ ሄዳለችና።

በኣሮጌዋ ካይሮ የሚገኝ ይዞታችን እንዲመሰረት ማድረጓ።

እናት ኄራኒ፥ በኣሮጌዋ ካይሮ የሚገኘውን ጥንታዊ ይዞታ ለማስመለስ፥ ብዙ ለፍታለች። ቦታው በጣም የቆሸሸና፣ የኑሮ ደረጃቸው በጣም ዝቅተኛ የሆነ ሰዎች የሚኖሩበት ነበር። ጣማፍ ከእነዚህ ችግረኛ ነዋሪዎች ጋር፣ ብዙ ጊዜ ወስዳና ተደራድራ፥ ወደ ተሻለ ቦታ እንዲዛወሩና አስፈላጊው ክፍያ እንዲፈጸምላቸው በማድረግ፥ ቦታውን ተረከበች። በዚህ ይዞታ ላይ ከነበሩት፥ የመጨረሻው ቤተሰብ፥ በ፲፬/፱/፹፬ ለቀቁ። ይህ ዕለት የኣባ ጳኩሚየስ የዕረፍቱ በዓል ንግሥ የሚከበርበት ነው። ሰኔ ፲፩ ቀን፥ ቦታው እንደ ተለቀቀ በኣፋጣኝ፣ ርዝመቱ ፬ ሜትር በሆነ ዐጥር ዙሪያው ታጥሮ የጽዳት ሥራው ተከናወነ። በኣንድ ወር ውስጥም ግንባታው ተጠናቀቀ። ይህ ወቅት፥ እናት ኄራኒ ሕመሟ የጸናበትና ወደ ሐኪም ቤት እየተመላለሰች የኬሞቴ ራፒ ክት

ትል ታደርግ የነበረበት ነው። እንዲሁም፥ የልብ ድካሚ በተደጋጋሚ ያስቃያት ስለ
ነበር፤ ለልብ ቀዶ ሕክምና ወደ አሜሪካ ለመሄድ በዝግጅት ላይ ነበረች።

ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም. ወደ አሜሪካ ሄዳ ቀ.ሕ. አደረገች። በዚህ ሁሉ
ችግር ማለፏ፤ ገዳሙን ከማስፋፋት አገልግሎቷ አላገዳትም። ባለችበት ሆና፥ በእሮ
ጌዋ ካይሮና በሲዲ-ሽሬይር ስላሉት ገዳማትና፤ አል-ኬሪያ ስለሚገኘው ጊዜያዊ ማረ
ፊያ ቤት ስለሚገጥመን ችግር ሁሉ፤ የመፍትሔ ሐሳቧን በስልክ አማካይነት ትለግ
ሰን ነበር። በኣንድ ወቅት የማዘጋጃ ቤት ሠራተኞች መጥተው፤ የግንባታ ሥራውን
ባለበት እንድናቆም አዘዙን። ይህ የተደረገው ወደ አሜሪካ በመሄጃዋ ዋዜማ በመ
ሆኑ፤ ማታውን ሰብስባን ከልብ በመነጨ ስሜት፥ እግዚአብሔር በሁሉም ነገር ይረዳ
ንና ጉዳዮችን ሁሉ እርሱ ራሱ ያከናውንልን ዘንድ ጸለይን። የእርስዋ ጭንቀት እኛ
ንም በዕንባ እንድንጸልይ አድርጎን ነበር።

አሜሪካ ከደረሰች በኋላም፤ ቀ.ሕ. እንዳጠናቀቀች፤ ስልክ ደውላ «በሦስቱም
መስክ» ስላለው ሁኔታ ትጠይቀንና ምክር ትሰጠን ነበር። የእግዚአብሔር ፈቃድ
ሆኖ፤ ችግሩም በመወገዱ፥ ሕልሟ እውን ሆኖ፤ የእምነቷ ጽናትም ፍሬ አፍርቶ፤
በዚያ ጥንታዊና አሮጌ ቦታ ላይ ብዙ በኣቶችን የያዘ የ«በ» ቅርፅ ያለው ባለ አራት
ፎቅ ሕንፃ ተገነባ። ከላይ ያሉት ሦስቱ ፎቆች፥ ዘጠና ስድስት በኣቶችን ሲይዙ፤ ምድር
ቤቱ ደግሞ፥ በቅዱስ ዮሴፍ ስም ቤተ ክርስቲያን ተደረገ። በሕንፃው ማዕከላዊ ክፍት
ቦታ ላይ፤ የሚመነጭ ውኃ ያለው ዐፀድ ተሠራ። የካቲት ፳፭ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.፥
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኑዳ ፫ኛ፤ ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት፥ አንባ ሩዊስ፤ አንባ ዮሐና
እና አንባ ዮናስ ጋር ተገኝተው፤ አዲሱን ሕንፃ መረቁ። በዚህ ጊዜ ብፁዕ አባታችን፤
የሕንፃውን ማማር «በሥነ ጥበብና ኪነ ሕንፃ በልዩ ጥንቃቄ የተሠራ» ብሎታል።

በዚህ ዕለት፥ እማሆይ አጋፕ በሓሬት ዙዋላ-ካይሮ የሚገኘው የቅ.ጊ.ሴ.ገ.፤
እማሆይ መርየም በሓሬት ዙዋላ-ካይሮ የሚገኘው የእመቤታችን የሴቶች ገዳምና
እማሆይ ዮሓና የኣሮጌዋ ካይሮ የቅዱስ ጊዮርጊስ የሴቶች ገዳም እመምኔቶች፤ ብዙ
ቊጥር ካላቸው መንፈሳዊ ልጆቻቸው ጋር ተገኝተው ነበር። በዚህ የገዳማችንን ልዩ
ታሪክ ባስመዘገበ ዕለት፤ ብፁዕ አባታችን፥ ታላቅ ደስታ ከገጽታው እየተነበበ፤ በዘ
ማሬ ሪቫኑን ቆርጦ፥ ቃለ ወንጌሉን በቃሉ እያነበበና፤ ሕንፃው ለዘለዓለም የእውነተኛ
በረከት ቦታ ይሆን ዘንድ እየጸለየ፤ በየክፍሎቹ ተዘዋውሮ ጠበል ረጨ።

ከዚሁ ሕንፃ ጋር የተያያዘ፤ ሌላ ባለ ሦስት ፎቅ ሕንፃም ተገንብቶ፤ የመጀመ
ሪያው ፎቅ ለመጋዘን፤ ሁለተኛው ፎቅ የ«ሀ» ቅርጽ ያለው ትልቅ የዕብነ በረድ ጠረ
ጴዛ ተደርጎለት፥ ለመመገቢያ አዳራሽ፤ ሦስተኛው ፎቅ ለመዓድ ቤት እንዲያገለግሉ
ሆነ። ከፊት ለፊቱ ባለው ዐፀድም የጀነሬተር ማስቀመጫ ተሠራለት። ከኣዲሱ በኣት
በኣንድ ወገን ደግሞ፤ ባለ ሁለት ፎቅ ሕንፃ ተገንብቶ፥ ምድር ቤቱ የምስል ወድምፅ

ቅጂዎች የሚቀመጡበት፤ የላይኛው ደግሞ፤ ከብረት የተሠሩ ተንቀሳቃሽ መደርደሪ
ያዎች ያሉት ቤተ መጻሕፍት ተደርጓል። ይህ ቤተ መጻሕፍት በዋናው ሕንፃ ውስጥ
ከሚገኘው ትልቅ ቤተ መጻሕፍት፥ በተጨማሪ የሚያገለግል ነው።

ዋናው ቤተ መጻሕፍት፤ በ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ዕድሳት ተደርጎ ተንቀሳቃሽ የብረት
መደርደሪያ ገብቶለታል። ኮምፒዩተርና የፎቶ ኮፒ መሣሪያ የተሟላለት ሲሆን፥ ልዩ
ልዩ መዝገበ ቃላትና ዐውደ ጥበብ[15]፤ የመረጃና የማጣቀሻ ጽሑፎችም፤ በዓረብኛና
ሌሎች ቋንቋዎች አሉት። ማንኛውንም ዐይነት የሕትመት ሥራዎች ስንሠራ፤ ይህንን
በኣንባቢው እጅ ያለውን መጽሓፍ ጨምሮ፥ ምንጫችን ይኸው ቤተ መጻሕፍታችን
ነው። ቤተ መጻሕፍቱን ምሉእ ለማድረግ፤ እማሆይ ኄራኒ ልዩ ትኵረት ሰጥታ
ሠርታለች። በእርሷ መሪነትና መካሪነት፤ በዓረብኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች፤ ብዙ
መጻሕፍት አሳትመናል። ለምሳሌ የሰማዕቱ ቅዱስ መርቆሬዎስ ገድል፤ በእርሱ አማ
ላጅነት በየዘመናቱ የተፈጸሙ ተኣምራት፤ የመነኰሳይያትና ሴት ለማዕታት ገድልና
ተኣምራት ይጠቀሳሉ።

እየተስፋፋ የመጣውን ገዳማዊ ሕይወት፤ በተጠናከረ ሁኔታ ለማስተናገድ ይቻል
ዘንድ፤ በ፲፱፻፺፩ ዓ.ም. ጣማፍ ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶችን የሚሰጡ፤ አራት ተጨማሪ
ሕንፃዎችን አስገንብታለች። አንዱ ባለ ሦስት ፎቅ ሕንፃ፤ በውስጡ ለተሳላሚዎች፤
ለጎብኚዎችና መነኰሳይያቱን ለሚጠይቁ፥ ማስተናገጃ አዳራሽ አለው። ሌላው ባለ
ሦስት ፎቅ ሕንፃ ለዕቃ ቤትነት ያገለግላል። ሦስተኛው ባለ አምስት ፎቅ የሆነው
ሕንፃ፥ ለተግባር ቤት የተዘጋጀ ሲሆን፦ የመጀመሪያው ፎቅ፥ የዕንጨት ሙያ ሥራ
ዎች፤ ሁለተኛው፥ የቆዳና የጨርቅ ሥፌት ሥራዎች፤ ሦስተኛው፥ የቊሳቊሶች ማስ
ዋቢያ የሆኑ ግብዓቶችን ማዘጋጃ፤ አራተኛውና አምስተኛው ደግሞ በኣንድነት፥ የጥ
ልፍ ሥራ መለማመጃዎች፥ ናቸው።

ከዚህ በኋላ፥ ሌላ ባለ ሦስት ፎቅ ሕንፃ በመታነፁና፤ ከኣንዱ ሕንፃ ወደ ሌላው
የሚደረገው እንቅስቃሴ ግርግር ከመፍጠሩና፤ በተለይ ለሕሙማንና ደካማ አረጋው
ያን አስቸጋሪ ከመሆኑም በተጨማሪ፥ ለመሳለምና ለጉብኝት፤ ለዕቃ ግዥ ወይም
በሌላ ምክንያት የሚመጣው ሕዝበ ክርስቲያን፤ ከመነኰሳይያቱ ጋር ሳይተያይና
ሳይተረማመስ መተላለፍ አስቸጋሪ ሆኖ ነበር። ስለዚህ በላይኛዎቹ ፎቆች ላይ፥ እያን
ዳንዱን ሕንፃ እርስ በእርስ የሚያገናኝ ድልድይ አሠራችለት። ከዚህ በኋላ፥ በማንኛ
ውም ምክንያት ከውጪ የሚመጣ ማንኛውም ሕዝበ ክርስቲያን፤ እንቅስቃሴውን
ሁሉ እዚያው ምድር ቤት ጨርሶ እንዲመለስ በመሆኑና፤ ወደ ሕንፃዎቹ የላይኛው
ክፍል የሚገባበት ምንም ምክንያት ስለሌለው፤ ከመነኰሳይያቱ ጋር እንዳይተያዩ
ለማድረግ የተሻለ አማራጭ ሆኗል።

[15] {ኢንሳይክሎፒዳ (encyclopedia)}

ዙና የሴቶች ገዳማት እንዲስፋፉ ታላቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። እኛም ሰማያዊው መንግሥት ምን ያህል ቅርቧ እንደ ነበረ፥ በዓይናችን ዐይተን ምስክር ሆነናል።

ይህ የግብፅ መነኰሳት ቊጥር መጨመር፣ የመላውን ዓለም ሕዝብ ትኲረት ስቧል። በውጪው ዓለም ገዳማት እየተዘጉና እየጠፉ ባሉበት በዚህ ዘመን፣ የግብፅ ገዳማት ቊጥር መጨመሩን፣ የታሪክ አጥኚዎች መስክረዋል። የጣማፍ ኄራኒ መን ፈሳዊ እንቅስቃሴ ትኲረቷን በመሳቡ፥ በመጨረሻዎቹ ሁለት ዐሠርት ዐመታት ውስጥ የተገኘችና በመልካም አርኣያነት የምትጠቀስ . . . በማለት፣ ስለ እርሷ የጻፈችውን ጀርመናዊት ተመራማሪት ጲጠርኔላ ቫን ዱርን ሐርደርን መጥቀስ ይቻላል።

የማይናወጠው የእናት ኄራኒ መንፈሳዊ ጽናት፣ በኢ-አማንያኑ ዘንድ ያለው ቅቡልነት፣ በሁለት ወገን እንደ ተሳለ ሰይፍ ነው። ይኸውም፥ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ሃይማኖት እውነተኛና ትክክለኛ መሆኑና፣ የቅዱሳንን አማላጅነት በግልጽ ማሳየቱ ነው። እንደ ጀርመናዊቷ ተመራማሪት ገለጻ፣ ጣማፍ «የብቁዓን መነኰሳት ሕይወት (ዘመን) እንደገና ነፍስ እንዲዘራና ሕጋዊ እንዲሆን አድርጋለች። መነኰሳይያት እንደ ዐቅመ ቢስ ሴት የሚቈጠሩበት ጊዜ አበቃ። ዛሬ ዛሬ በተመስጦና በብቃት የሚ ያገለግሉ መነኰሳይያት፣ ቤተሰብ ካፈሩትና ልጅ ከወለዱት አንስት አንሰው ወይም በዝቅተኛነት አይታዩም»[17] ስትል አወድሳታለች።

ጣማፍ ኄራኒ፥ መነኰሳይያቱ የእጅ ሥራዎችን እንዲሠሩ የምታበረታቸው፣ ራሳቸውን እንዲችሉ ለማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ የሥራው ውጤት ተሽጦ፣ ረዳት የሌ ላቸውን ወገኖች መርጃ እንዲሆን ጭምር ነው። የሥራቸው ውጤት፥ በአንድ በኩል ችግረኛን መርዳት ሲያስችላቸው፣ በሌላ በኩል ደግሞ «መነኰሳይያት የሰው እጅ አይተው የሚኖሩና ውጤት የሌላቸው ናቸው» ብለው የሚያስቡ ሰዎችን፣ ወይም የማኅበረሰቡን ክፍሎች አፍ የሚያስይዝ ነው።

ጀርመናዊቷ ዱርን ሐርደር፣ በጣማፍ የኣመራር ችሎታ ውስጥ፣ ሌላው ትኲ ረቷን የሳበው ነጥብ፣ ወጣት አንስት ለኣመክሮ ሲመጡ፣ ከመካከላቸው ከፍተኛ የት ምህርት ደረጃ ያላቸው መገኘታቸው ነው። ለመነኰሳይያት የትምህርት ደረጃ ከፍ ተኛ መሆን በተደረገው ጥረት፣ የኣንበሳውን ድርሻ የምትይዘው ብቸኛ ሰው እማሆይ ኄራኒ ናት። በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም.፥ ወደ ገዳማችን የመጣ አንድ ጎብኚ እንደ ዘገበው፥ «ከመ ነኰሳይያቱ መካከል፥ በተለያየ ሙያ የተመረቁ ሐኪሞችና (ስፔሻሊስቶች) ተዋንያን ይገኙበታል» ብሏል።

[17] ተመራማሪዋ ጲጠርኔላ፥ Contemporary Coptic Nuns የተሰኘውን ጽሑፏን ማዘጋጀት የጀመረችው ፲፱፻፰ዎቹ መጀ መሪያ ላይ ነው። ስለዚህ በጽሑፏ ላይ «የመጨረሻዎቹ ሁለት ዐሥርት ዓመታት ስትል ፲፱፻፷ እና ፲፱፻፰ ዎቹን ማለቷ ነው።

እኛም ብንሆን፥ የሥራ ድልድላችን ካላስገደደን በስተቀር፥ ማለትም በጥበቃ፣ በመስተንግዶ፣ ወይም በሽያጭ ሥራ ካልተሠማራን፣ ወደ ምድር ቤት የምንወርድ በት ምክንያት ስለሌለን፣ ከሕዝብ ጋር የመተረማመስ ችግራችን ተወግዶ፣ አገልግሎ ታችንን በትኲረት እንፈጽም ዘንድ አመቺ ሆኖልናል። ይህ ሁሉ አርኪ ፍሬ የሚያ ሳየን፣ የእናት ኄራኒን አርቆ አሳቢነት፣ አስተዋይ ነት፣ ቀናነት፣ ባሰበችው ነገር ላይ ሁሉ ውጤታማ፣ ቡሩካን እጆቿ የነኩት ነገር ሁሉ፥ ፍሬው የሚያምርና እማ መላ መሆኗን ነው። የኣምላካችን የእግዚአብሔር ስም የተመሰገነ ይሁን፣ አሜን።

ስል-ካናትር ስል-ኼይሪያ።

በማኑፌያ ክፍለ ሀገር፥ በሻታኑፍና ዳርዋ ወረዳ፣ ስል-ካናትር ስል-ኼይሪያ በተባለ አካባቢ፥ እናታችን ኄራኒ ስምንት አክር ከዐሥራ ሁለት ካራት መሬት ገዝታ፣ ሦስተኛው አቡ ሰይፊን የሴቶች አንድነት ገዳም ተገደመ። ዘመኑም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሲኑዳ ፫ኛ በፐትርክና የተሾመበት ነው። ቦታው ጸጥታ የሰፈነበትና ካይሮ ለሚገኘው ለ«እናት» ገዳማችን ቀረብ ያለ ነው። የመጀመሪያዎቹ መነኰሳይያት፥ በ፳፭፻/፪/ፎቷ ወደዚህ አዲስ ገዳም ገቡ። በ፲፱፹፬ ዓ.ም. ሐምሌ መጀመሪያ ላይ አራት ሜትር ከፍታ ያለው ዐጥር ተገነባ። ግንቦት አጋማሽ ላይ ፲፱፹፯ ዓ.ም.፥ ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል፣ የ«በ» ቅርፅ ያለው ሕንፃ ታነጸ። በጊቢው አብዛኛው ክፍል፥ የተምር ዛፎች፣ ሌሎች ትልልቅ ዛፎችና ለማር ምርት የሚያገለግሉ አበቦች የተተ ከሉ ሲሆን፣ ለከብት እርባታና ለሸክላ ሥራ አገልግሎት የዋለ ቦታም አለው።

በበዓለ ሻም አል-ነሲም[16] የኣርጌዋ ካይሮ የቅ.ጊ.ሴ.ገ. እመምኔት፥ እማሆይ ዩኦና ከመንፈስ ልጆቿ ጋር፣ በየዓመቱ ወደ አል-ካናትር አል-ኼይሪያ ገዳም መጥታ፥ ከጣ ማፍ ጋር መልካም ጊዜን ያሳልፋሉ። በዚህ ዕለት ጣማፍ ዕጓለ ማውታንን ሰብስባ፣ ይህን መንፈሳዊ በዓል ከእኛ ጋር እንዲያከብሩና ተደስተው እንዲውሉ ትጋብዛቸዋለች።

ገዳማዊ ሕይወትን ማስጌጥ፣ ማሳደግ፣ ማጎልበት።

«ዘይትህ መልካም መዓዛ አለው፣ ስምህ እንደሚፈስስ ዘይት ነው፣ ስለዚህ ደናግል ወደዱህ» (መኃ. ፩፥፫)። ስሙ ቅዱስ የሆነ እግዚአብሔር፣ እናታችን ኄራኒ በምታደርገው ነገር ሁሉ፥ ሞገስ ሆኗታል። የእናታችን ነፍስ፥ በእውነት ወደ እግዚአብሔር ፍቅር በሚያ ቀርብ፥ በሰማያዊ ጥበብ የተዋበች ናት። ይህ ሽታው እንደ መልካም ዕጣን የሚናኝ፣ ጣዕሙ እንደ መልካም ዘይት የሆነ ግሩም ግብሯ፥ ብዙዎችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሙሽሮች ወደ መሆን አምጥቷል። በግብፅ ገዳማት ውስጥ፣ መነኰሳይያት እንዲህ

[16] Sham el Nessim በቅብጥ ቤተ ክርስቲያን የሚከበርና ልዩ ትኲረት የሚሰጠው በዓል ነው። በዓሉ የሚከ ረው፥ በትንሣኤ ማግስት በሚውለው ሰኞ ነው። ይኸውም፦ {በኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ዘንድ፥ ማዕዶት ይባላ ለው ነው}።

ሌሎች ገዳማትም ይህን አርኣያ ለመከተልና፤ የከፍተኛ ትምህርት ምሩቅ የሆኑ ምሁራንን እየተቀበሉ ለማመንኮስ ጊዜ አልፈጀባቸውም። በቀደሙት መነኮሳ ይያትና በኣሁኖቹ መካከል ያለው የትምህርት ደረጃ ልዩነት፥ የትየለሌ መሆኑ ለዚህ በቂ ማስረጃ ነው። ቀደምቱ መነኮሳይያት የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ ከመሆኑም ሌላ፤ ብዙዎቹ መበለታትና አካለ ስንኩላን ናቸው። በተቃራኒው የኣሁኖቹ፤ አብዛኛ ዎቹ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምሩቃን ናቸው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቄርሎስ ፮ኛ፥ በ፲ ዙር ፲፫ ወጣንያንን አመንኩሷል። ከእርሱ በኋላ ደግሞ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኑዳ ፫ኛ፤ እስከ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም. ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ፤ ወደ ገዳማችን ባደረ ጋቸው አራት ይፋ ጉብኝቶች፥ ፸፮ ወጣንያንን አመንኩሷል። ብፁዕ አባታችን በግዞት በነበረባቸው ዘመናት፤ ከ፲፱፻፶፬-፶፮ ዓ.ም. ምንም ዐይነት ሥርዓተ ምንኩስና ሳይፈጸም ቆይቷል።

በእነዚህ የኣቡኑ የግዞት ዓመታት፥ እናታችን ኄራኒ በጸሎት፤ በዕንባና ስግደት የእግዚአብሔርን ምሕረት ስትለምን ቆይታለች። ያ ሁሉ የጤና ዕጦት ችግር ሳያን ሳት፤ የበኣቷን መስኮት ላለመክፈትና ንጹሕ አየር ላለማግኘት ፍጹም ውሳኔ አድርጋ ነበር። በግዞት ያሉትን አባቶች መከራ በማሰብና፤ ችግራቸውን ትጋራቸው ዘንድ፤ በደከማት ጊዜ እንኳን አካሏን የምታሳርፈው፤ ግድግዳ ደገፍ ብላ በመቆም፤ ወይም ባዶ መሬት ላይ በመተኛት ነበር። በዚህ ተጋድሎዋ፥ ምግብም አየርም በበቂ መጠን ባለማግኘቷ ምክንያት፤ ዐቅሟ ደክሞ ለኮሌራ በሽታ ተጋልጣለች። በዚህ ምክንያት፥ ወደ ላይም ወደ ታችም እያላት በመሰቃየቷ ድካሟ የከፋ ነበር።

ይህም ሆኖ፥ ቀንም ሆነ ማታ ከእኛ ጋር እየተገኘች፤ የጸሎቱን ሥርዓት በጥ ንካሬ ከመምራት አልተቆጠበችም። ለሱባኤና ሥርዓተ ቅዳሴ ለመፈጸም የሚመጡ አባቶችንም በትጋት ታስተናግዳለች። በዚህ የችግር ዘመን፤ ታሳይ ስለ ነበረው ጥን ካሬ፤ አንድ አባት እንዲህ ብሏል፥ አቡነ ሺኑዳ ፫ኛ ከተሾመ በኋላ፤ ፕሬዚደንት ሳዳት በግዞት አስቀምጦት በነበረ ጊዜ፥ ጣማፍ ኄራኒ ሕዝበ ክርስቲያኑን ለማረጋጋትና፤ በጸሎት ለመሳተፍ ለሚፈልግ ሁሉ፤ የገዳሙን በር በመክፈት ታላቅ ተሳትፎ አድር ጋለች። በየሳምንቱ ሐሙስ ለጸሎት በዚያ መሰባሰብ ሰንጀምር፤ መነኮሳይያቱን እያ ተጋች ሁሌም በዝማሬ ይቀበሉናል። በእርሷ መሪነት በኣንድነት ሆነው ዳዊት ይደግ ማሉ። ለጸሎት የሚመጡት አባቶች ቍጥርም ከዕለት ወደ ዕለት በመጨመሩ፤ ብዛ ታችን እስከ ሰልሳ አምስት ደርሶ ነበር። በእርሷ የጸሎት በረከት ብፁዕ ወቅዱስ አባ ታችን ከግዞት ተመልሰ፥ በደስታ ተቀብለነዋል። ስለ ቤተ ክርስቲያንና፤ የቤተ ክርስቲ ያን ራስ ስለ ሆነው ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያላት ጽኑ ፍቅር፤ ወደ ገዳሙ ለመሳለም የሚመጣውን ሕዝበ ክርስቲያን ሁሉ የሚማርክ ነበር።

ጣማፍ ወጣንያንን ተቀብሎ ከማስተማርና ማመንኮስ፤ እንዲሁም ነባሩን ከመንከባከብ ሌላ፤ እመምኔቶችንም መርጣ እንዲሾሙ ታደርግ ነበር። ከመጀመሪያ

ዎቹ ደቀ መዛሙርቶቿ አንዷ የሆነችውን፤ እማሆይ ዮሳናን በኣሮጌዋ ካይሮ ለሚገ ኘው የቅ.ጊ.ሴ.ገ. በእመምኔትነት መርጣ፤ በብፁዕ አቡነ ሺኑዳ ፫ኛ አንብሮተ እድ እን ድትሾም አድርጋለች።

በዚያ በመከራ ዘመን፤ ለእግዚአብሔር ከምታቀርበው ጸሎት ተሳክቶልን በመ ቅረፀ ድምፅ ያስቀረነው ቀጥሎ ያሉትን ብቻ ነው፦

† ፈጣሪዬ ሆይ! በዚህ የመከራ ዘመን፤ ቤተ ክርስቲያንህን በምሕረት ዐይኖችህ ጎብ ኖት። እንደ ቸርነትህ እንጂ እንደ በደላችን አይሁን። ክቡር ደምህን አፍስሰህ ያዳ ንሽን ማደሪያዎችህ ነንና።

† ቤተ ክርስቲያንህን አሁን አድን! በማይታይ ጎይልህ አባታችን አቡነ ሺኑዳን ታደ ገው! ዓለሙን ሁሉ በንጹሓን እጆችህ የያዝህ ሆይ! ሕይወታችንን ታደጋት። የሓ ሰት መልእክተኞችን ከእኛ አርቅልን።

† ገባሬ ሠናያት የሆንህ ጌታዬ ሆይ! ለጻጻሳቱ አንደበት ሁናቸው። ዓለሙንና በው ስጡ ያለውን ሁሉ የፈጠርህ፤ የኣማልክት አምላክ፤ የነገሥታት ንጉሥ ሆይ! የእኛ ዕውቀት ከምንም አያድነንም። የተንኰል ጉባኤያቸውን፤ የጥፋት ዓላማቸ ውን ለውጠህ ለቤተ ክርስቲያን የሚበጃትን ነገር አድርግ።

† ፓትርያርካችንን በቀና መንገድ ምራው፤ ቤተ ክርስቲያንንም ከሰይጣን ፈተና ታደ ጋት። ክቡር ደምህን አፍስሰህ የዋጀሃትን ቤተ ክርስቲያን ፈጥነህ ናና አድናት።

† ብዙ ተኣምራትን የምታደርግ፤ ገባሬ መንክራት የሆንህ ጌታዬ ሆይ! ክቡር ደም ህን አፍስሰህ የዋጀሃትን ቤተ ክርስቲያን እንዲሁ አትተዋት። ምንም እንኳን፥ የሥጋዊ ምኞታችንና የኀጢኣታችን ብዛቱ፤ ወደ አንተ ባያቀርበንም፤ ቸርነትህንና ፍቅርህን ተስፋ እናደርጋለንና አንተ ቅረበን።

† አቤቱ ቤተ ክርስቲያናችንን እንደማትተዋት፤ ቅን አገልጋይህን ብፁዕ ወቅዱስ አባታ ችንንም እንደማትረሳው እናምናለን። ፓትርያርኩ የምድር መልእክተኛህ ነውና፥ በመከራው ጊዜ ድረስለት። በሰላምና በጤና ወደ መንበሩ መልሰው። ከእርሱ ጋር በግ ዞት ያሉትን ጳጳሳት፤ ሊቃነ ካህናትና ቀሳውስትም አስባቸው። ለዓለመዓለም አሜን!

ጣማፍ ለፓትርያርኩ ያላት ፍቅር፤ የጌታን እግር በሽቱ እንደ ቀባችው ሴት ነው። «ይህንን ፍቅሯን» በእኛ ልብ ውስጥ ተክላ፥ የታማኝነትንና የመሥዋዕትነትን ውን እያጠጣች አለምልማዋለች።

ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን በገዞት ሳሰ፥ ጣማፍ ጌራኒ የዳፈችሰት ደብዳቤዎች።

ሯ) **ሰብፁዕ ወቅዱስ አባታችን፥ አቡነ ሲኑዳ ፫ኛ፣ ፓትርያርክ ዘመንበረ ማርቆስ፦** ብፁዕ አባቴ! በቅድሚያ በፊትሁ ተንበርክኬ፣ ንጹሕ እጆችዎን ስሜ፥ በረከትዎን አባኝ ዘንድ ይሁንልኝ! አሜን። አጠገብዎ ተገኝቼ ለእርስዎ ያለኝን አክብሮትና ፍቅር ልገልጽልዎ እመኛለሁ። እርስዎ ለቤተ ክርስቲያናችን፣ ለገዳማቱና ለመንፈስ ልጆችዎ፣ እንዲሁም ለሁሉም ሕዝበ ክርስቲያን መልካምና እውነተኛ እረኛ ነዎት። ብፁዕ አባቴ! እንዴት አሉ? በጥሩ ጤንነት እንደሚገኙ ተስፋ አደርጋለሁ።

ሷ) **ሰጋሱ አባቴ!** የብፁዕነትዎ ልብ፥ ሁሉ ዘንድ መድረስ የሚችል፥ ትልቅና ደግ፣ በዕድሜ የገፋም ወጣትም፣ ጠንካራም ደካማም እንደ ሆነ እረዳለሁ። በእርስዎ ውስጥ ለወጣንያኑም ሆነ ለመነኰሳይያቱ መልካም ምሳሌ ይመነጫል። ልግስና፣ ትዕግሥትን፣ ፍቅርን፣ ይቅር ባይነትን፣ ጥንካሬን፣ ትሕትናንና ራስን መሠዋትን አሳይተውናል። ስለ ቤተ ክርስቲያን ደኅንነት ጸልየዋል፣ የልጆችዎን መከራ ተሸክመዋል። ቸር እግዚአብሔር፣ ሰማዕታቱና ቅዱሳኑ ሁሉ ከእርስዎ ጋር አሉ።

ቿ) **ሩኅሩኑና ውዱ አባቴ!** በመስከረም ፫ ፲፱፻፫፬ ዓ.ም. በሥጋም፣ በነፍስም፣ በመንፈስም፣ ከባድ ድካምና ተስፋ መቍረጥ ተሰምቶኝ ነበር። ስለ እርስዎ ደኅንነትና ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰላም ስል፥ ሰማዕቱ አቡ ሰይፊንን አምርሬ ወቀስሁት። ለሁለት ቀናት ከኣልጋ መውረድ ባለ መቻሌ፣ በሓኪም እርዳታና በመድኃኒት አጋዥነት ቆየሁ። ምግቤም «ጉልኮስ» ብቻ ነበር።

በዚያ ሁሉ ሕመም ውስጥ እያለሁ፣ አቡ ሰይፊንን አየሁት። አንድ ትልቅና አንድ ትንሽ የሆኑ ሁለት ፍሬዎችን ሰጥቶኝ፥ «ብዪውና ትፈወሻለሽ!» አለኝ። እኔም ትንሹን ፍሬ ተቀበልሁትና፥ ለእኔ ይሄ ይበቃኛል፣ ለምንድር ነው እናንተ በእንደዚህ ዐይነት የከፋ ሁኔታ የምትተዉን? ስለው፣ «እኛ አልተውናችሁም። ነገር ግን ይህ ፈተና የመጣባችሁ፥ በጥቂት አገልጋዮችና ምእመናን መካከል በመጣ ትዕቢት ምክንያት ነው። አሁንም ንስሐ ሊገቡ፣ በደላቸውን ሊናዘዙ ይገባቸዋል። እነዚያ ትሑታኑ፣ ለጋሶቹና ጽኑዓኑ ደግሞ፥ ጸጋ እግዚአብሔርን ያገኙ ዘንድ ይህ ሆኗል። በጸሎት ጽኚ፣ ታጋሽ ሁኚ እንጂ፥ አትጨነቂ። ፓትርያርኩን እግዚአብሔር በተአምራቱ ወደ ቦታው ይመልሰዋል» ካለኝ በኋላ፥ ሌሎችም ብዙ ጉዳዮችን ነግሮኛል። ሆኖም በእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ካይሮ ሲመጡ በኣካል ተገናኝተን ብነግርዎ እመርጣለሁ።

ቀ) **በሁሉ ታላቅ የሆኑ አባቴ!** እርስዎን በሕልሜ ሁለት ጊዜ አይቼዎታለሁ። የመጀመሪያው በ፳፬ ዓ.ም. ጷግሜን ውስጥ ሲሆን፥ ብስጭት ብለው የሆነ ነገር እየጠበቁ ነበር። ሁለተኛውን ሕልም ያየሁት ደግሞ፥ ባለፈው ሳምንት ነው። በዚህኛው

ሕልሜ የተሻለ ሁኔታ ነበረዎት። እኔም ይህን በማየቴ በጣም ተረጋጋሁ። ብፁዕ አባቴ! ስለ እርስዎ ሁኔታ የሚነግረን ሰው አልነበረም ብልዎት ያምኑኛል? ስለ እርስዎ የሰማነው፥ ከሁለት ቀናት በፊት በኣባ አርቄሊደስ አማካይነት ነው።

ቈ) **ደግና አዛኝ አባቴ!** በልባችን፣ በሕሊናችን፣ በጸሎታችን ሁሉ፥ ቀንም ሆነ ማታ ተለይተውን አያውቁም። እግዚአብሔር ስለ እኛና ስለ ቤተ ክርስቲያን ሲል፣ እርስዎን ደህና ያድርግልን። ዕድሜዎትን ለዘመናት ያርዝምልን። በወላዲተ አምላክ ምልጃ፣ በቅዱሳኑና በእርስዎ ጸሎት፣ እግዚአብሔር ጠላት ዲያብሎስን በእግርዎ ሥር ያስገዛልዎት። ሁሉም መነኰሳይያት እኔም ጭምር፣ ቡሩካን እጆችዎን እንስማለን፣ በጸሎትዎ ያሳስቡልን።

አክባሪ ልጅዎት ጌራኒ መርቆሬዎስ።

ምዕራፍ ስራት

ድል ከነሡት ዳዲቃን ጋር፥ በኣንድነት የመንዝ ክብር።

«የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሯችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥ የኑሮኣቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ ምሰሉኣቸው»፣ «ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል፣ አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል»፥ (ራእ.፫፩፥፭፣ ዕብ.፲፫፥፯)።

በበሽታ የሚገኝ ጸጋ፦ «እርሱም፦ ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኀይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ። እንግዲህ የክርስቶስ ኀይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ» እንዲል ቅዱስ መጽሓፍ፥ ክብርት እናታችን እማሆይ ጌራኒ፥ የድኅነት ወደብ ላይ ለመድረስ ሩጫዋን ሁሉ በገድል ፈጽማለች። ገድሏም ለክብር የሚያበቃ ሆኖላታል (፪ኛ ቆሮ.፲፪፥፱)። የምር እንግድነት ጊዜዋ እስኪያበቃ ድረስ፣ የልብ መሻቷ ይፈጸምላት ዘንድ፥ ራሷን ንፁሕ መሥዋዕት አድርጋ በማቅረብ፣ ዕለት ዕለት እንደ ጧፍ እያበራች፣ እንደ ሻማ እየቀለጠች ኖራ፣ ድል በመንሣት ሰማያዊ መንግሥቱን ወራሽ ሆነች።

ቅዱሳን መላእክቱም፥ ይህንን መሥዋዕት መልካም መዓዛ እንዳለው ዕጣን ተቀብለው፣ ወደ ሰማያዊው መንበር አደረሱላት። የጌቶች ጌታ፣ የነገሥታት ነጉሥ የሆነ፥ ፈጣሪኣችን ባወረሳት ክብርና ሞገስ ነፍሷን አጅበው አሳረጉት። «ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥ ሌሊትም ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል። . . . በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፣ እግዚአብሔርም ዕንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል። . . . እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም» እንዲል (ራእ.፯፥፲፭/፲፯፣ ፲፪፥፲፩)።